በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ. 241469
ቀን ፡- ሕዳር 27 ቀን 2016 ዓ/ም

ዳኞች- እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሀብታሙ እርቅይሁን

አመልካች ፡- አለምሰገድ ተወልደ------------- ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ወ/ሮ ደመቀች ታደሰ ------------ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሳሽ፤ ተጠሪ ተከሳሽ ሆነው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በ09/09/2013 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ሟች አባቴ አቶ ተወልደ ተ/ሚካኤል ከተጠሪ ጋር ሕይወታቸው እስካለፈ ድረስ በትዳር የኖሩ ሲሆን፤ ተጠሪ ከአባቴ ጋር በመሆን እንደ እናት ሆነው አሳድገውኛል፡፡ ተጠሪ እና ሟች አባቴ በአዳማ ከተማ ቢ.ቃ ቀበሌ 500 ካ/ሜ ቤት በአባቴ ስም የተመዘገበውን አፍርተው ነበር፡፡ እኔ ኤርትራ ለሥራ ሄጄ ባለሁበት ጊዜ አባቴ በ1998 ዓ/ም እንዳረፉ የአባቴ ወራሽ መሆኔን አረጋግጫለሁ፡፡ ተጠሪ በአባቴ ስም ተመዝግቦ የነበረውን ይህንን የጋራ ቤት ሸጠው በአዳማ ከተማ እሬቻ ቀበሌ የሚገኝ ሌላ 250 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ቤት የካርታ ቁጥር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

11908/2002 እንደገዙ ተረድቻለሁ፡፡ በመሆኑም በአባቴ ስም ተመዝግቦ የነበረውን እና 500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት በጨረታ በገቢያ ዋጋ የሚያወጣው ተጣርቶ 50 % ተጠሪ እንዲከፍሉኝ፤ ይህ ማይሆን ከሆነ በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው የካርታ ቁጥር 11908/202 በአባቴ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት ተሽጦ በተገኘው እና የጋራ ገንዘባቸውን ጨምረው የገዙት ስለሆነ ፍርድ ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ በማድረግ 50 % እንድካፈል እንዲፈረድልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም በ03/10/2013 ዓ/ም ባቀረቡት የመከላከያ መልስ እኔ እና ሟች በትዳር አብረን እያለን ሟች በ1998 ዓ/ም ባደረባቸው ህመም ምክንያት አርፈዋል፡፡ ተጠሪ በቀበሌ ቤት ውስጥ ለብቻዬ ስኖር መጠጥ በመሸጥ ስተዳደር ቆይቼ ከጊዜ በኋላ ስለደከመኝ ከመጠጥ ሽያጩ ሳገኝ ከነበረው ገቢ እና አጠቃላይ የመጠጥ እቃዎቼን በመሸጥ ጨምሬበት 2009 ዓ/ም በአዳማ ከተማ ኢሬቻ ቀበሌ የሚገኘውን 250 ካ/ሜ ላይ ያረፈ ካርታ ቁጥሩ 11908/2002 በስሜ የተመዘገበውን የመኖሪያ ቤት በግል ገንዘቤ አፍርቼ ያለኝ እንጂ ከሟች ጋር ስንኖር በጋራ ያፈራነውን ንብረት በመሸጥ የገዛሁት ቤት ስላልሆነ ክሱ ውድቅ እንዲደረግልኝ፡፡ ተጠሪ እና ሟች የአመልካች አባት በአዳማ ከተማ ቢቃ ቀበሌ ያፈራነውን ካርታ ቁጥር 7115/96 480 ካ/ሜ ላይ ያረፈ የመኖሪያ ቤት በ29/07/1996 ዓ/ም በብር 80000 ሽጬው ገንዘቡን ለቤት ውስጥ ወጪ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ በመሆኑም አመልካች የሟችን ድርሻ ብር 40000 እንዲወስዱ ስነግራቸው ፈቃደኛ ስላልሆኑ፣ አለአግባብ ለመበልጸግ በማሰብ የግል ንብረቴ የሆነውን ሟች ካረፉ በኋላ በግል ገንዘቤ ያፈራሁትን ልታካፍይኝ ይገባል በማለት የመሰረቱት ክስ አግባብነት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአዳማ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤቱም የግራቀኙን ምስክሮች መርምሮ ተጠሪ የሚኖሩበትን በኢሬቻ ቀበሌ የሚገኘውን በ250 ካ/ሜ መሬት ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ከሟች አባት ጋር በጋራ ያፈሩትን ንብረት 500 ካ/ሜ ላይ ያረፈውን የመኖሪያ ቤት ሽጠው የገዙት ሳይሆን የአመልካች አባት ካረፉ በኋላ ከተለያዩ የግሮሰሪ ንግድ ገቢዎች የገዙት፤ የግል ንብረታቸው፤ ከውርስ ንብረት ጋር ያልተቀላቀለ መሆኑን መረዳት ተችሏል፤ በመሆኑም አመልካች 250 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት የአባቴን ድርሻ 50 % ተጠሪ ያካፍሉኝ በማለት የጠየቁት ዳኝነት የህግ አግባብ ያለው አይደለም፤ የሚካፈሉት መብት የላቸውም፡፡ በሌላ በኩል በቢቂ ቀበሌ የሚገኘውን 480 ካ/ሜ ላይ ያረፈ መኖሪያ ቤት ተጠሪ በ29/07/1996 ዓ/ም መሸጣቸውን፣ ተጠሪ እራሳቸው ቤቱን በብር 80000 እንደሸጡ ያልካዱ ሲሆን አመልካች ድርሻቸውን ብር 40000 ይውሰዱ ብለዋል፡፡ አመልካች በ1996 ዓ/ም የተሸጠውን ቤት ወደ ኋላ ተመልሶ የጠየቀበት ዳኝነት ተቀባይነት የለውም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያላቸው መብት የቀድሞው ቤት ከተሸጠበት ብር 80000 ውስጥ ድርሻቸውን ብር 40000 ሊወስዱ ይገባል፡፡ በተጨማሪም አመልካች ለተጠሪ የውርስ ንብረቱን እንዲያስተዳድሩ እና የሟችን ድርሻ እንዲቀበሉ ውክልና መስጠታቸው ስለተረጋገጠ አመልካች አሁን ወደ ኋላ ተመልሰው ተጠሪ ቤቱን ሽጡት በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካች የይግባኝ አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡትን የይግባኝ አቤቱታ ፍርድ ቤቱ መርምሮ በክርክር ውስጥ የአመልካች አባት እና የተጠሪ መኖሪያ ቤት የተሸጠ እና በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኝ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ተጠሪ የውርስ ንብረቱን እንዲያስተዳድሩላቸው ውክልና የሰጧቸው መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች የጋራ ንብረት የሽያጭ ውሉን ህገ ወጥ ነው በማለት ተቃውመው ባላስረዙበት በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኘው ቤት በጫረታ በወቅታዊ ዋጋው ተሽጦ ድርሻዬ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ዳኝነት የህግ ድጋፍ የለውም፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ከተያዘው ጭብጥ አንጻር አመልካች ከላዩ መብት ያለው ንብረት ለ3ኛ ወገን የተላለፈበት ውል ፍርስ ባልተደረገበት አመልካች በስር ፍርድ ቤት የሚጠይቁት ዳኝነት አግባብነት የሌለው ስለሆነ ችሎቱ ከዚህ ነጥብ አኳያ የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ የሚተችበት አግባብ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ከግሮሰሪ በተገኘ ገቢ፣ በዕርዳታ እና በብድር ቤቱን መግዛታቸውን ስላረጋገጡ ንብረቱ ሟች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ትዳር በሞት ከፈረሰ በኋላ የተፈራ ስልሆነ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ክስ በሚሰማበት ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች በድርሻቸው ላይ ብር 20000 ጨምረው ለመስጠት ተስማምተው ባለበት ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ብር 40000 ብቻ እንዲከፍሉ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ለአመልካች ብር 60000 ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

ይሕ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ አመልካች በ24/05/2015 ዓ/ም በጻፉት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በግልጽ የጠየኩትን ዳኝነት ወደጎን በመተው ያልተጠየቀው ዳኝነት ላይ የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡ ይህ ንብረት በጨረታ ይሸጥልኝ ብዬ የጠየኩት አንድም ዳኝነት የለም፤ እኔ የጠየኩት ተጠሪ ከውርስ ድርሻዬ 50 % ከሆነው ላይ ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ከፍቃዴ ውጭ ስለሸጡብኝ፤ ባይሸጡብኝ ኖሮ በአሁኑ ሰዓት ከዚህ ንብረት ላይ የማገኘው ጥቅም በጊዜው የገቢያ ሁኔታ በገንዘብ እንዲከፍሉኝ ነው እንጂ ከ2-3 ጊዜ በሽያጭ ለ3ኛ ወገን የተላለፈን ቤት እንዲሸጥልኝ የሚል ባልሆነበት ሁኔታ ከክርክር ውጪ በመውጣት የስር ፍርድ ቤቶች የወሰኑት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፤ የሰበር ውሳኔ መዝገብ ቁጥር 40510ን ያላገናዘበ ስለሆነ እንዲሻርልኝ፡፡ አመልካች እየጠየኩ ያለሁት መብት የውርስ ንብረቱ የገበያ ዋጋ በአሁን ጊዜ የገቢያ ዋጋ እንጂ በ1996 ዓ/ም ተጠሪ በሚሉት እንዳልሆነ ከክርክሬ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በ1989 ዓ/ም አባቱ እንደሞተ ወራሽነቴን ካረጋገጥኩ በኋላ ለተጠሪ የውክልና ስልጣን ተጠሪ እንደኔ ሆነው 50 % ድርሻዬን እንዲያስተዳድሩልኝ ወይም እንዲጠብቁልኝ በፍ/ብ/ህ/ቁ 2199 እና 2204 መሰረት ውክልና ሰጠዋቸው እንጂ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2205 መሰረት ያልወከልኳቸው መሆኑን በስር ፍርድ ቤት ከቀረበው ማስረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ ትክክለኛውን የውርስ ንብረት ዋጋ በመደበቅ ነው ብር 80000 ያሉት፡፡ የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች በግልጽ የጠየኩትን ዳኝነት በዝምታ አልፈው የሰጡት ውሳኔ ስህተት ነው፡፡ የንብረት አጣ ተሹሞልኝ፣ 500 ካ/ሜ ላይ ያረፈው ቤት በኋላም 480 ካ/ሜ ሆኖ የተጻፈው ካርታ ተጠሪ የውርስ ንብረት ድርሻዬን ጨምሮ በ1996 ዓ/ም ውስጥ በጊዜያዊ የገቢያ ዋጋ ስንት እንደሚያወጣ፤ በ1996 ስንት ተሸጠ ምን ያህል እንደሚያወጣ ግምቱ ተጣርቶ ከወጣ በኋላ ተጠሪ 50 % እንዲከፍሉኝ እንዲፈረድልኝ ዳኝነት የጠየኩ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መሆኔን ክሴን ማየቱ በቂ ነው፡፡ ከጋራ ንግድ እና ሥራ ከግሮሰሪ ቤት በተጠሪ የተሰበሰበ እስከ 1989 አባቴ እስካረፉበት ያለው ተሰልቶ ተጠሪ ድርሻዬን 50 % ከባንክ ወለዱ ጭምር እንዲከፍሉኝ ጠይቄ ባለበት የስር ፍርድ ቤቶች ይህንንም ጥያቄ ውስቅ በማድረግ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ እና በጥያቄዬ መሰረት ተጣርቶ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ ችሎት ታይቶ ለአመልካች አከራካሪው ቤት በ1996 ዓ/ም የተሸጠበትን ዋጋ ግማሽ እንዲከፈላቸው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የጠየቁትን ዳኝነት ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በአብለጫ ድምጽ ታዟል፡፡ ተጠሪ በ28/10/2014 ዓ/ም በተጻፈ የመከላከያ መልስ የቀበሌ አስተዳደሩ ችግሬን እና ብቸኝነቴን በማየት ልኖርበት የምችለውን የቀበሌ ቤት በስሜ መዝግቦ ሰጥቶኝ እየኖርኩበት የነበረ ሲሆን መጠጥ በመሸጥ በማገኘው ገቢ ስተዳደር የነበረ ሲሆን ከሟች ጋር እንደ ባልና ሚስት በ1970 ዓ/ም አብረን መኖር ጀምረናል፡፡ ከሟች ጋር በአዳማ ከተማ ቀበሌ ቢቃ ውስጥ የጨረቃ መሬት ይዘን 2 ክፍል ጭቃ ቤት ሠርተንበት እየኖርን እያለ ሟች ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን ከዚህ በኋላ ይህ ጨረቃ ቤት በስሜ ተመዝግቦ በ1996 ዓ/ም ህጋዊ ሆኖ በካርታ ቁጥር 7115/96 ሆኖ ተሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በኋላ ተሯሩጬ መሥራት ሲከብደኝ በ29/07/1996 ዓ/ም ይህንን 2 ክፍል ጭቃ ቤት በብር 80,000 በጊዜው የገበያ ዋጋ የሸጥኩ ሲሆን ከአመልካች ጋር ግን መገናኘት ያልቻልን ሲሆን በህይወት መኖር እና አለመኖራቸውን መለየት ስላቻልኩ ቤቱን ሽጬ የሽያጭ ውሉ ተመዝግቦ፣ የባለይዞታነት ስም ወደ ገገር ተዘዋውሮ ያለ ሲሆን አመልካች ከሽያጭ ገንዘቡ ውስጥ ብር 40,000 እንዲወስዱ ብጠይቃቸውም ፈቃደኛ ባለመሆን አለአግባብ ለመበልጸግ አስበው እየተከራከረ ስለሆነ ቅሬታቸው ውድቅ ሊደረግልኝ ይገባል፡፡ ቤቱ የተሸጠው በዚያን ጊዜ የሚያወጣው ዋጋ ተገምቶ ነው፡፡ የተሸጠው ቤት ዘመናዊ ሆኖ ቪላ ቤት ተሰርቶበት ባለበት አመልካች በአሁን ጊዜ የገቢያ ዋጋ ይገመትልኝ የሚሉት 2 ክፍል ጭቃ መኖሪያ ቤት ስለሌለ እና መገመት ስለማይችል አመልካች የሚጠይቁት ዳኝነት አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ መጠጥ የመሸጥ ሥራን እየሠራው የምኖረው ከሟች ጋር ሳንገናኝ በፊትም ስለነበር እሳቸው ካረፉ በኋላም ሥራውን ስሠራ የነበርኩ እና የግል ሥራዬ ስለሆነ አመልካች ከዚህ የአልኮል መጠጥ ሽያጭ ያገኘሁትን ገቢ እንዳካፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በአዳማ ከተማ እሬቻ ቀበሌ ውስጥ በ2002 ዓ/ም መኖሪያ ቤት ሰርቼ እየኖርኩበት ያለሁት ይህንን መኖሪያ ቤት ሙሉ እድሜዬን ጉልበት ባለኝ ጊዜ የአልኮል መጠጥ እየነገድኩ እንዲሁም ተጨማሪ ሥራዎችን ሰዎች ቤት እየሰራሁ ገንዘብ አጠራቅሜ፣ ዘመዶቼ ረድተውኝ የሠራሁት እና አከራይቼ እየተዳደርኩበት ያለ አዲስ ቤት እንጂ የቀድሞው ቤት ስላልሆነ አመልካች ያቀረቡት ቅሬታ ውድቅ እንዲደረግልኝ እና የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በ14/11/2015 ዓ/ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ጉዳዩ የውርስ ንብረት ድርሻን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ እስከ ኦሮሚያ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ደርሶ አመልካች የአባታቸው ንብረት ድርሻ ብር 60,000.00 እንዲከፈላቸው ተወስኗል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3/ሀ) ላይ በግልጽ እንደተመለከተዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት ነዉ? ወይም አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ መቼ ነዉ? የሚለዉን ጽንሰ ሃሳብ አስመልክቶ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በበርካታ መዛግብት ላይ በሰጠዉ ዉሳኔ አመላካች መስፈርቶችን ለማስቀመጥ የሞከረ ቢሆንም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በህግ ደረጃ ወጥ የሆነ ትርጓሜ አልተሰጠዉም ነበር፡፡ ይሁንና ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ የዋለዉ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜ ይሰጣል፡፡ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተግባራቸዉን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ዉጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽ እና ተገማች በሆነ ሁኔታ እንዲያከናዉኑ ማድረግን አንዱ ዓላማዉ ያደረገዉ ይህ አዋጅ ካካተታቸዉ አዳዲስ ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ለሚለዉ ጽንሰ ሃሳብ ትርጓሜ መስጠቱ እና በክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታይ የሚችልበትን ሁኔታ አስመልክቶ የተለየ ድንጋጌ ማካተቱ ነዉ፡፡ በአዋጁ በትርጉም ክፍል አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች መገንዘብ እንደሚቻለዉ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፣ ህግ ያላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለዉን ህግ የሚጠቅስ፣ ለክርክሩ አግባብነት ያለዉ ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለዉ ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፣ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ዉድቅ በማድረግ የተወሰነ፣ በፍርድ አፈፃፀም ሂደት ከዋናዉ ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትዕዛዝ የተሰጠበት፣ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተወሰነ፣ የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠዉ ዉሳኔ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ በመቃረን የተወሰነ ሲሆን ነዉ፡፡

በመሆኑም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በሚል የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ ጉዳይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ለማለት የሚቻለዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ በዝርዝር ከተመለከቱት ሁኔታዎች ዉስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድጋጌዎች የምንገነዘበዉ ነዉ፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ዉሳኔ ሲሆን አቤቱታዉ የቀረበዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ/ም (አንቀጽ 58 ይመለከቷል)፣ በኋላ በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረቡትን የውርስ ንብረት ድርሻ ክርክር የሥር ፍርድ ቤቶች በመመልከት የአመልካች አባት እና የተጠሪ መኖሪያ ቤት የተሸጠ እና በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኝ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች ወራሽነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ተጠሪ የውርስ ንብረቱን እንዲያስተዳድሩላቸው ውክልና የሰጧቸው መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካች የጋራ ንብረት የሽያጭ ውሉን ህገ ወጥ ነው በማለት ተቃውመው ባላሰረዙበት በ3ኛ ወገን እጅ የሚገኘው ቤት በጫረታ በወቅታዊ ዋጋው ተሸጦ ድርሻዬ እንዲወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ዳኝነት የህግ ድጋፍ የለውም፣ተጠሪ ከግሮሰሪ በተገኘ ገቢ፣ በዕርዳታ እና በብድር ቤቱን መግዛታቸውን ስላረጋገጡ ንብረቱ ሟች ከተጠሪ ጋር የነበራቸው ትዳር በሞት ከፈረሰ በኋላ የተፈራ ሰልሆነ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በሌላ በኩል ክስ በሚሰማበት ጊዜ ተጠሪ ለአመልካች በድርሻቸው ላይ ብር 20000 ጨምረው ለመስጠት ተስማምተው ባለበት ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ብር 40000 ብቻ እንዲከፍሉ መወሰኑ አግባብ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማሻሻል ተጠሪ ለአመልካች ብር 60000 ይክፈሉ በማለት የተሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10(1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ውሳኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 406851 ህዳር 03 ቀን 2015 ዓ/ም የሠጠው በሰበር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1)(ሀ) መሰረት ፀንቷል፡

2. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

ትዕዛዝ

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !